# ማጠቃለያ

## የሪፖርት ማጠቃለያ

የSound Transit የBoeing Access Road Station ፕሮጀክት በTukwila ውስጥ በSouth Boeing Access Road፣ East Marginal Way እና Interstate 5 (I-5) አቅራቢያ በሚገኘው የLink ቀላል ባቡር ኔትወርክ 1 መስመር ላይ አዲስ ከፍ ያለ ጣቢያን የሚጨምር ይሆናል። ይህ የጣቢያ ቦታ በመራጮች በተፈቀደው Sound Transit 3 (ST3) ስርዓት እቅድ ውስጥ ተካትቷል።

Sound Transit ከማህበረሰቡ አባላት ጋር ለመነጋገር በርካታ የተሳትፎ ተግባራትን አድርጓል።

ከማርች እስከ ሜይ 2024፣ ሰባት የማህበረሰብ ቃለ መጠይቆችን አድርገናል። የእነዚህ ቃለመጠይቆች ግብ የፕሮጀክት መረጃን ማጋራት፣ ከአካባቢው ማህበረሰቦች ጋር ግንኙነት መፍጠር እና የማህበረሰብ ተሳትፎ እና የግንኙነት እቅድን ማሳወቅነበር። ከማህበረሰብ አባላት እና ከማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር ተነጋግረናል። በቃለ መጠይቁ ወቅት ሰዎች፣ ቁልፍ መዳረሻዎች ላይ የአውቶቡስ ግንኙነቶች እና የሸትል አቅርቦት እንዲኖር በማድረግ ወደ ጣቢያው የሚደረገው ጉዞ ቀላል እንዲሆን ያላቸውን ፍላጎት አካፍለዋል።

ከጁላይ 2 እስከ ጁላይ 28 ድረስ የመስመር ላይ ክፍት የዳሰሳ ጥናት አዘጋጅተናል። የመስመር ላይ ክፍት ጥናት የጣቢያ ምርጫን ጨምሮ የፕሮጀክት መረጃን አጋርቷል። የዳሰሳ ጥናቱ አላማ በማህበረሰቡ አባላት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች እና ስጋቶች ላይ ግብአት ለመሰብሰብ ነበር። የዳሰሳ ጥናቱ የተካሄደው በ279 ሰዎች ላይ ነበር።

- **279 ሰዎች** ከጁላይ 2 እስከ ጁላይ 28 ድረስ **የመስመር ላይ የዳሰሳ ጥናቱን** አጠናቀዋል
- **127 ሰዎች** የፕሮጀክት ዝመናዎች እንዲደርሷቸው ተመዝግበዋል
- **በአካል በተዘጋጀ ክፍት የውውይት ላይ** ከ**45 በላይ ሰዎች** ጋር ተነጋግረናል
- በ**2 በአካል መገኘት የሚጠይቁ የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይቶች ዝግጅቶች** ላይ ከ**80 በላይ ሰዎች** ጋር ተነጋግረናል
- በ**7 የማህበረሰብ ቃለ መጠይቆች** እና **አጭር መግለጫዎች** ላይ ከሰዎች ጋር ተገናኝተናል
- **6,012 ፖስታዎችን** በፕሮጀክቱ አካባቢ በ**1 ማይል** ራዲየስ ውስጥ ለሚገኙ ተቀባዮች ተልከዋል
- በማህበራዊ ሚዲያ **30,350 ስሜቶች ተገልጸዋል** እንዲሁም **1,720 ጠቅታዎችን** ተመዝግበዋል

የዳሰሳ ጥናት ሰጭዎች ለእግረኛ፣ ቢስክሌት ወይም ትራንዚት ለሚያደርጉ ሰዎች የተሻሻለ ተደራሽነት እና ደህንነት አስፈላጊ የንድፍ ጉዳዮች መሆናቸውን እንዲሁም ሰዎች ወደ ጣቢያው በቀላሉ እንዲደርሱ እንደሚያደርጉ ተናግረዋል። ምላሽ ሰጪዎችም የጣቢያው ንድፍ የግንባታውን የቆይታ ጊዜ እና አሁን ያለውን የቀላል ባቡር አገልግሎት መስተጓጎል መቀነስ እንዳለበት ጠቁመዋል። ምላሽ ሰጪዎች የመኪና ማቆሚያ ቦታን ማሳደግ በንድፍ ውስጥ ሊካተት የሚገባ አስፈላጊ ነገር መሆኑንም ጠቁመዋል።

ከመስመር ላይ ክፍት ጥናት ጎንለጎን Sound Transit በአካል መገኘትን የሚጠይቅ ክፍት ጥናትን እና የሁለት ጠረጴዛ ዝግጅቶችን አዘጋጅቷል። በእነዚህ ዝግጅቶች ላይ ሰራተኞቹ ከ125 በላይ ሰዎች ጋር ተገናኝተዋል።

የዝግጅቱ ተሳታፊዎች በBoeing Access Road፣ East Marginal Way እና I-5 አካባቢ ላለው ጣቢያ አጠቃላይ ድጋፍ ሰጥተዋል። ብዙ ሰዎች East Marginal Way ላይ የታቀደው ጣቢያ ምርጫቸው እንደሆነ አጋርተዋል። የአውቶብስ ግንኙነቶች መዘርጋትን እና የአየር ሁኔታን መከላከልን ጨምሮ በጣቢያው ላሉ እና ወደ ጣቢያው የሚጓዙ ሰዎች ሰላም፣ ደህንነት እንዲሁም የተሳለጠ መንገድ እንዲኖራቸው ቅድሚያ ተሰጥቶ ሊሰራ ይገባል ሲሉ ተሰብሳቢዎቹ ተናግረዋል። በተጨማሪም ሰዎች በጣቢያው ውስጥ የመኪና ማቆሚያ እንዲሁም የመጫኛ እና ማውረጃ ቦታ እንዲኖር ፍላጎት እንዳላቸው ሰምተናል።

በአቅራቢያ ወደሚገኙ ቤቶች እና ንግዶች ፖስታዎችን በመላክ፣ ለማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶችን ኢሜይል በመላክ፣ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በመለጠፍ እና በአካባቢው ንግዶች እና የማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታዎች ላይ በራሪ ወረቀቶችን በመለጠፍ

የክፍት ውይይት ዝግጅቶችን አስተዋውቀናል እንዲሁም ስለ ፕሮጀክቱ ያለውን ግንዛቤን ከፍ አድርገናል። የፕሮጀክቱ የሚዲያ ሽፋን እና የተሳትፎ እድል በThe Urbanist ላይ ወጥቷል።

የማህበረሰብ አስተያየት፣ ግምት ውስጥ መግባት ካለባቸው ቴክኒካል ጉዳዮች ጋር አብሮ በመሆን፣ በዚህ ፕሮጀክት እንዲሁም በፅንሰ-ሃሳባዊ ምህንድስና/በአካባቢያዊ ግምገማው እንዴት እንደምንቀጥል ሀሳብ ይሰጠናል። በዚህ አመት መጨረሻ፣ ከማህበረሰቡ የተሰማውን ወቅታዊ መረጃ እናቀርባለን።